## ማርያም በስምሽ (1)

ማርያም በስምሽ ይዘናል ቀናና
ትንሣኤሽን ልጅሽ ያሳየናልና
ጾም ማለት እንግዲህ ይኸው ነው ሥርዐቱ
ሐዋርያት ጾመው ለኛ አበረከቱ
ነፍስና ሥጋችን በመብል ተጣልተው
ሽማግሌ ሆኖ ጾም እስታረቃቸው
አብረው እያደሩ አብረው እየዋሉ
አያምርም አይመስልም በመብል ሲጣሉ
ነፍሳችን ከሥጋ መለየቷን እውቃ
የዓለም ተድላዋን ደስታዋን ንቃ
በጾም በሱባዔ ትኖራለች ታጥቃ
ነፍስም ለሥጋዋ ትነግረው ጀመረች፣
በብዙ ምሳሌ እያመሳሰለች
ሥጋዬ ሞኝ ነህ መብልን አትውደደው
ከአዳም እንስቶ ከመጀመሪያው ሰው
መብል ሲጎዳ እንጂ ሲጠቅም መች አየነው (2)።

## የሲና ሐመልማል (2)

የሲና ሐመልማል የሙሴ ጽላት[፪]
የሲሎንዲስ ጥበብ ሰፀ መድኃኒት[፪]
አሁን በምን በምን እንመስልሻለን[፪]
አፁብ ድንቅ እያልን እናወድስሻለን[፪]
የአረጋዊ ፍጥረታት የታደሱብሽ[፪]
የሕይወት መሰላል ማርያም አንቺ ነሽ[፪]
አዝ...
የነቢያት ትንቢት የልባችን ተስፋ[፪]
በአንቺ መመኪያነት ማኅበራችን ይስፋ[፪]
አዝ...
በአንቺ መመኪያነት ኦርቶዶክስ ይስፋፋ
ተዋሕዶ ይስፋፋ
አዝ...

## ለማርያም እንዘምራለን (3)

ለማርያም[፪] እንዘምራለን ለዘለዓለም[፪]
የተዘጋች በር ለዘለዓለም ሕዝቅኤል ብሏል ለዘለዓለም
ንጽሕት ናት በእውነት ለዘለዓለም በፍጹም ድንግል ለዘለዓለም
እብነት አድርገን ለዘለዓለም እኛም እርሱን ለዘለዓለም
በፍጹም ፍቅር እንዘምራለን[፪]
አዝ...
የዋህት ርግብ ለዘለዓለም ሰላም አብሣሪ ለዘለዓለም
ለጨለማ ሕይወቴ ለዘለዓለም ብርሃንን አብሪ ለዘለዓለም
አማፀንሻለሁ ለዘለዓለም ድንግል ለነፍሴ ለዘለዓለም
አደራ ቅድስት አንቺ ነሽ ዋሴ[፪]
አዝ...
እጅግ የበዛ ነው ለዘለዓለም ያለኝ ፍቅር ለዘለዓለም
አይወሰንም ለዘለዓለም አይነገርም ለዘለዓለም
በእርሷ ደስ ይለኛል ለዘለዓለም ጎሜት አደርጋለሁ ለዘለዓለም
ስሟን እየጠራሁ እዘምራለሁ[፪]
አዝ...
ነዪ ነዪ ስላት ለዘለዓለም ቀንና ሌሊት ለዘለዓለም
አትለየኝም ለዘለዓለም ለእኔስ ቅርቤ ናት ለዘለዓለም
አፁብ አፁብ ብለው ለዘለዓለም አመስገኗት ለዘለዓለም
ክብሯን ሲገልጹ ሲያጥራቸው ቃላት[፪]
አዝ...

## ድንግል አመቤቴ (4)

ድንግል እመቤቴ የዓለም እናት (2)
አንቺን የመረጠ ይክበር መለኮት (2)
ካንቺ ተወለደ ወንኑን ሊዋጅ (2)
ቀዳማዊ ቃሉ የእግዚአብሔር አብ ልጅ (2)
ኤፍሬም በውዳሴው ያመሰገነሽ (2)
ደመና ኤልያስ ድንግል አንቺ ነሽ (2)
የምሕረትን ዝናብ ያስገኘሽልን (2)
በሲኦል በረሃ እንዳንኮነን (2)
ያሬድ በመዝሙሩ የዘመረልሽ (2)
ዕሪቱ ደመና ንጽሕት አንቺ ነሽ (2)

## ታማልደናለች (5)

ታማልደናለች[፪] ማርያም[፪] ቤዛዊት ዓለም
ሚካኤል በክንፉ ገብርኤል በፋና
ያወጡናል[፪] ከሲኦል ፈተና

## ድንግል ወላዲተ ቃል (6)

ድንግል[፪] ወላዲተ ቃል
እሟሟትሽ በጥር በነሐሴ መቃብር ድንግል
የእንቺስ ለብቻ ነው ትንሣኤሽ ሲነገር
ሥጋሽ በምድር ላይ የታለ እንደ ፍጡር
ዐርጓል ወደ ሰማይ ከክርስቶስ መንበር
አዝ...
ሥጋሽን ሲያሳርጉ መላእክተ ሰማይ ድንግል
ቶማስ በደመና ሲመጣ መንገድ ላይ
መግነዝ ተረከበ ለሐዋርያት ሲያሳይ
አዝ...
ትንሣኤሽን ሽተው ግራ ሲገባቸው ድንግል
ሐዋርያት ጾመው ተገለጽሽላቸው
ተቀብራ አልቀረችም በምድር ከዶጂ
ወደላይ ዐረገች እኛም እንደልጂ
አዝ...
ለማየት ሲጓጉ የድንግልን ትንሣኤ ድንግል
ዕርገቷን አወቁ በንጹሕ ጉባኤ
እኛም እንጸልይ ደጃችንን እንዝጋ
ከወላዲት አምላክ እንድናገኝ ዋጋ
አዝ...

## ፩. ቡርክት አንቲ (7)

ቡርክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ ኢየሱስ (2)
ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ መድኃኔ ዓለም ።
ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ አማኑኤል ።
ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ ሰአሊ ለነ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ድንግል ሆይ በለእንቺ (8)

ድንግል ሆይ በለእንቺ ነውና መሐሪ
እማልጅን ከአንድ ልጅሽ ከፈጣሪ
በሙን እንዳልጠራ እንደበትም የለኝ
ፊቱንም እንዳላይ ሥራዬ አሳፈረኝ
እዝ...
ታውቆኛል ጥፋቴ ብዙ እንደበደልኩ
ትእዛዙን እንደሻርኩ ሕጉን እንደጣሰኩኝ
አንተ ክቡር መልአክ ልደቱን አብሣሪ
አማልደኝ ከጌታዬ ከፈጣሪ
እዝ...
በፊቱ እንዳላፍር የተጠራሁ ለታ
አለምንቀበሁ ከአሁኑ ይቅርታ
ጻድቃን ሰማዕታት እናንተ ሁላችሁ
አማልዱኝ ከአምላኬ ከአምላካችሁ
እዝ...

## ነይ ነይ ነይ ድንግል ማርያም (9)

ነይ ነይ ነይ ድንግል ማርያም
አጽናኝና አማላጅ ተሰፋዬም ሁኚ ለዘለዓለም፣
ጋጪአቱ በዝቶ የበደሌ ሸክም በጣም የከበደ
እሮኻለሁኝ ካንቺ ሥጋን ነስቶ ወደ ተዋሃደ
ነይ ነይ ነይ ድንግል ማርያም
አጽናኝና አማላጅ ተሰፋዬም ሁኚ ለዘለዓለም
ከገነትና ከመንግሥተ ሰማይ ተሰደን
እንዳንቀር ስለወደደ፣
ቅዱስ የእግዚአብሔር በግ፣ በተራራችን ላይ
ለኛ ቢል ታረደ
ነይ ነይ ነይ ድንግል ማርያም
አጽናኝና አማላጅ ተሰፋዬም ሁኚ ለዘለዓለም
አዳምን ለማዳን ንጹሕ መሥዋዕትን
እንዲሰዋ ስለፈቀደ
መሐሪ ይቅር ባይ በቤተልሔም በረት
ለኛ ተወለደ
ነይ ነይ ነይ ድንግል ማርያም
አጽናኝና አማላጅ ተሰፋዬም ሁኚ ለዘለዓለም።

## ይቄድሰዋ (10)

ይቄድሰዋ መላእክት[፪] ለማርያም
በውስተ ውሳጤ መንጦላእት ወይብልዋ
በሐኪ ማርያም ሐዳስዩ ጣዕዋ

በመጋረጃ ውስጥ መላእክት ማርያምን ያመሰግኗታል
ሰላምታ ይገባሻል ማርያም አዲሲቷ እንዞሳ እያሉ

## እመቤታችን ማርያም (11)

እመቤታችን ማርያም ሀገራችንን ጠብቂልን በምልጃሽ
እመቤታችን ማርያም ኢትዮጵያን ጠብቂልን በምልጃሽ
ከመናፍቃን ከከሃዲያን ከጠላት ሰይጣን መውረሽ
እንድትጠብቂያት በምልጃሽ

## የማን የማን (12)

የማን የማን የማን ሕይወት
አንቺ ነሽ ኪዳነ ምሕረት (2)
ቅድስት እመቤቱ የአምላክ እናት
ሆነሽ የተገኘሽ ንጽህት ቅድስት
አንቺ ነሽ (2) ኪዳነ ምሕረት (2)
የማን .................
**አብ እሳት ወልድ እሳት መንፈስ ቅዱስ <u>እሳት</u>**
እባክህ ክርስቶስ ይህችን ቀን ቀድሳት
አንቺነሽ (2) ኪዳነ ምሕረት
የማን....................
የቢና ሐመልማል የሰው ልጅ ሕይወት
አንቺን የመረጠ ይክበር መለኮት
አንቺ ነሽ (2) ኪዳነ ምሕረት
የማን...................
አዘክሪ ድንግል ለልጅሽ በእውነት
በደህና እንዲያደርሰን ለመጪው ዓመት
አንቺ ነሽ (2) ኪዳነ ምህረት
የማን ....................

## ስብሐት ለአብ (13)

ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ
ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ
ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስም
ምስጋና ከማቅረብ <u>ከቶ እንወሰንም</u> (2)
ዛሬም ወደፊትም ደግሞም ለዘለዓለም
ስብሐት ለአብ .....
ከዚህ ከማራኪ ከኃላፊው ዓለም
የጠራ ይድናል <u>የፈጣሪውን ስም</u> (2)
በእውነት ያለሐሰት ያለጥርጥርም
ስብሐት ለአብ ........
ከቶ መድኃኒቱን የሚጠላ የለም
ኑሯችን እንዲያምር <u>አንድነታችንም</u> (2)
ሊኖረን ይገባል ፍቅርና ሰላም
ስብሐት ለአብ ........
አቤቱ አምላክ ሆይ እንለምንሃለን
እንድትገኝልን <u>በመካከላችን</u> (2)
ይኸው ተገኝተናል ሁለት ሦሥት ሆነን።
ስብሐት ለአብ .........
ያልከውን አስበህ እናንተ ሁላችሁ
ስሜን ከጠራችሁ ሁለት ሦሥት ሁናችሁ (2)
እኔም እገኛለሁ በመካከላችሁ
ስብሐት ለአብ ..........

## ኪዳንኪዮነ (14)

ኪዳንኪዮን (3)
ኪዳነምሕረት (2)
ለኃጥአን ቤዛነ ለኃጥአን ተሰፋነ
ኪዳንኪዮን (2)

www.ethiopianorthodox.org

## ድንግል እመቤቱ (15)

ድንግል እመቤቴ የዓለም እናት
አንቺን የመረጠ ይከበር መለኮት
ከአንቺ ተወለደ ወገኑን ሊዋጅ
ተዳማዊ ቃሉ የእግዚአብሔር አብ ልጅ
ኤፍሬም በውዳሴ ያመሰገንሽ
ደመና ኤልያስ ድንግል አንቺ ነሽ
የምሕረትን ዝናብ ያስገኘሽልን
በሲኦል በረሀ እንዳንከኙነን
ያሬድ በመዝሙሩ የዘመረልሽ
ራቁ ደመና ድንግል አንቺ ነሽ

## ድንግል ላወድስሽ (16)

ድንግል ላወድስሽ በኤፍሬም ውዳሴ
አለኝታ ልበልሽ በሥጋም በነፍሴ
እንደ ዕዝራ ስምሽን ልጠምር
እንደ ያሬድ በዜማ ልደርድር
ታካችና አሰልቺ ንግግር ይቅርና
እንደበቴን ይሙላው በድንግል ምስጋና
ላወድስሽ በእምነት እያየሁሽ
አለኝታዬ አዛኝ ልበልሽ
እዝ...
አንገቴን ቢያስደፉኝ በደሌ ተጭኖኝ
አጽናናስሁ በአንቺ ስምሽን እያሰብኩኝ
ብፍገመገም ለመውደቅ ብቃረብ
በአንቺ ይመከል እንካሳው የእኔ ልብ
እዝ...
መላእክት ነቢያት እንዳመሰገኑሽ
ቅዱሳን አባቶች በፍቅር እንደጠሩሽ
የአምላክ እናት ንጽሕት ነሽ እያልኩኝ
ላመሰግንሽ ስለሰምሽ ልቀኝ
እዝ...

## የዓለም ንግሥት የሆንሽው (17)

የዓለም ንግሥት የሆንሽው ድንግል ማርያም እናቴ
ታመሰግንሽ አንቺን ሁልጊዜ ሕይወቴ
ማርያም ባርኪኝ እመቤቴ እሰግድ ለኪ
እንዳልንገላታ ጠብቂኝ በኃጢአት ዓለም ጎዳና
ደግሞም እንድመገብ በማያዊ መና
ማርያም የአዳም ጤና <u>እሰግድ ለኪ</u>
ተሸጬ ስኖር ልጅሽ በኃጢአት ከተማ ዓለም
የሚያወጣኝ ጠፍቶ የእናት ልጅ ወንድም
ወጣሁኝ በልጅሽ ደም <u>እሰግድ ለኪ</u>
ከቅድስት ሀገር ከቤተልሔም ተንሥተሽ
ምድረ ግብጽ አውራጃ ፈጥንሽ ስትደርሺ
ማርያም መከራን አየሽ <u>እሰግድ ለኪ</u>
ያ ምቀኛ ሰይጣን ንጉሥ ተንኮል የተመላው ሄሮድስ
ልጅሽን ሊገድለው ደሙንም ለማፍሰስ
ተሯሯጠ በእግር በፈረስ <u>እሰግድ ለኪ</u>
የአንቺ መንገላታት ሁልጊዜ ያሳዝነኛል ሲወራ
በምድረ ግብጽ ሁሉ ያየሽው መከራ
ማርያም ነፍሴን አደራ <u>እሰግድ ለኪ</u>

## የብርሃን መውጫ (18)

የብርሃን መውጫ የሕይወት መሰላል
የተነበየላት ነቢዩ ሕዝቅኤል[፪]
የሰለሞን አክሊል የአሮን በትር
ሆና የተገኘች የአምላክ ማኅደር[፪]
የዳዊት መሰንቆ የጌዲዎን ጸምር
በገነት መካከል ያለች ለምለም ሣር
አፍርታለችና ያለወንድ ዘር
እሰቲ እናመስግናት እንዲህ በማለት
ቅድስት እናታችን ሰብሕት ወቡርክት
እንቀጸ ብርሃን ማዕርገ ሕይወት
አዘክሪ ድንግል ለልጅሽ በእውነት
በደኅና እንዲያደርሰን ለመጪው ዓመት[፪]
እንድናገኝ ፍቅርን እንደ ሐዋርያት
እንደ እመቤታችን እርምም ትዕግሥት
ያድለን ፈጣሪ ፍጹም መድኃኒት

## ሰላም ሰላም ማርያም ድንግል (19)

ሰላም ሰላም (2) ማርያም ድንግል
ልመናሽ ለሚያምኑት ድኅነት ያሰጣል (2)
ደቀ መዛሙርቱ በሐዛብ ሲዋኙ
ይኸው በቅርብ ቀን ምልክት አገኙ
ሰላም ሰላም .... ....
ለኛ ለልጆችሽ ኃጢአት ላይከመን
ከልጅሽ ይቅርታን ድንግል ለምኝልን
ሰላም ሰላም ......
በሐና በኢያቄም እመቤታችን
በዚህች ቀን ባርኪልን ስብሰባችንን
ሰላም ሰላም ... ...

## ሰላም ለኪ (20)

ሰላም ለኪ እምነ ጽዮን
ማርያም ውድስት የሕይወት ብርሃን
ሰላም ለኪ እምነ ጽዮን
ሰላም ልበል ተንበርክኬ
በብፅዕናሽ ተማርኬ
መርከበ ኖኅ አዳራሽ
ሰላም ለኪ ልበልሽ
እዝ...
ድንግል የአብርሃም ድንኳን
ሰላም ሰላም ሐረገወይን
ያዕቆብ ያየሽ መሰላል
የሰሎሞን ክብር አክሊል
እዝ...
ጽላተ ሙሴ የእሪት
የአሮን በትር መድኃኒት
የዋህ ርግብ የኢያቄም
የነቢያት ተስፋ የአዳም
እዝ...
እሳተ መለኮትን የያዝሽ
ምሉዕ አምላክን የወሰንሽ
ቤተ መቅደስ የልዑል
ሰላም ለኪ እመ ወድንግል
እዝ...

## በሰላም ንዒ ማርያም (21)

በሰላም ንዒ[፪] ማርያም
ትናገዘኒ[፪] ኀዘን ልብየ
በሰላም ንዒ[፪] ማርያም
ምስለ ሚካኤል[፪] ወገብርኤል
እዝ...
ምስለ ሱራፌል[፪] ወኪሩቤል
እዝ...
ምስለ ሁርኤል[፪] ወሩፋኤል
እዝ...
ምስለ ኩሎሙ[፪] ቅዱሳን
እዝ...
ምስለ ወልድኪ[፪] አማኑኤል
በሰላም ንዒ ማርያም

## የዓለም መድኃኒት (22)

የዓለም መድኃኒት ድንግል ወለተ ኢያቄም ወሃና
ላንቺ ይሁን ላንቺ ክብርና ምስጋና(2)
ተቋመ ማኅቶት ድንግል የኃጥአን ምድር አለኝታ
ችግር እንዳይገጥመን በላይኛው ቦታ
ቃል ኪዳንሽ ለኛ ይሁነን መከታ
የዓለም ፀሐይ ድንግል ከልልተ ሞገስ ወግርማ
ቦታችን እንዲሆን ከጻድቃን ከተማ
እርቂልን ከኛ ያን ከባድ ጨለማ
የማሕፀንሽ ፍሬ ክርስቶስ ንጉሠ ሰማይ ወምድር
አንቺን መርጦ ላንቺ ሰለሰጠሽ ክብር
ቀለለልን ለኛ የችግር ቀንበር
ምልዕተ ምሕረት ወተስፋ የዓለም ቤዛ ድንግል
ጻድቃን በበረሃ በዱር በገደል
ያለቅሳሉ ካንቺ እንዲያገኙ ኃይል።

## ሰላም የታቦር ተራራ (23)

ሰላም ሰላም (2) የታቦር ተራራ
ብርሃን መለኮት ባንቺ ላይ አበራ (2)

ሙሴና ኤልያስ እንዲያ ሲሸበሩ
ምነው አንቺ አልፈራሽ ምንድነው ምሥጢሩ

ሰላም ሰላም … …

ደቀ መዛሙርቱ ከርሱ ጋር የሞሉ
የአምላክን ድምፅ ሰምተው
ለመጽናት አልቻሉም

ሰላም ሰላም … …

## በደብረ ታቦር (24)

በደብረ (2) በደብረ ታቦር (2)
ሰባሕኩከ በደብረ (2)

ትርጉም፦ በታቦር ተራራ አመሰገንኩህ

## ለማን በለማን (25)

አማን በአማን (2)
ተሰብሐ በደብረታቦር

ትርጉም፦ በእውነት በደብረታቦር ክበረ፡
ተመሰገነ

## የታቦር ተራራ (26)

የታቦር ተራራ በጣም ደስ ይበልሽ (2)
አምላክ መለኮቱን ስለገለጠብሽ (2)

## ወተወለጠ (27)

ወተወለጠ ራእዩ በቅድሜሆሙ (2)
ወአልባሲሁኒ (5) ኮነ ፀዓዳ ከመበረድ

ትርጉም፦ በፊታቸው መልኩ በራ! ልብሱም
እንደበረዶ ነጭ ሆነ (አማረ)

## እመቤቴ ማርያም (28)

እመቤቴ ማርያም አለምንሻለሁ
በለቅሶ በዋይታ ፊትሽ ወድቄአለሁ
እመቤቴ ስሚኝ ተማፅኘሻለሁ[፪]
ኀዘኑ በዛብኝ ፈተናው ከበደኝ
እንደምን ልቻለው እኔስ ብቻዬን ነኝ
የአማኑኤል እናት ፈጥነሽ ድረሽልኝ[፪]
የልቤን ትካዜ ለማን እነግራለሁ
ችግሬን ጉዳቱን ለማን አዋያለሁ
እመቤቴ ስሚኝ ተማፅኘሻለሁ[፪]
በጣም ተንገዳገድኩ ልወድቅ ነው እኔ
እመ አምላክ ደግፊኝ ቁሚልኝ ከጎኔ

## በስመ ዚአከ (29)

በስመ ዚአከ ይትፌሥሑ ዮም (2)
ታቦር ወአርሞንኤም (4)

ትርጉም፦ ታቦርና አርሞንኤም በስምህ ደስ
ይላቸዋል።

## ታቦር ወአርሞንኤም (30)

ታቦር ወአርሞንኤም (4)
በስመዚአከ ይትፌሥሑ ዮም
ታቦር ወአርሞን-ኤም (2)

ትርጉም፦ ታቦርና አርሞንኤም ዛሬ በስምህ ደስ
ይላቸዋል።

## በሔዋን ምክንያት (31)

ኧኸ በሔዋን ምክንያት[፪] የተዘጋው ደጅ
ዳግም ተከፈተ[፫] በማርያም ልጅ[፪]
ኧኸ በሔዋን ምክንያት[፪] ከአምላክ ተጣልተን
በድንግል ማርያም[፫] ጽድቅን ተጎናጸፍን
ኧኸ ሔዋን ያመጣችው[፪] የነፍስ መከራ
ተደመሰሰልን[፫] በማርያም ሥራ
ኧኸ እናተ መላእክት[፪] እመቤታችን
ከአምላካችን ጋራ[፫] ድንግል አማልጅን[፪]
ኧኸ ትንቢተ ነቢያት[፪] እመቤታችን
የመንፈስን ምሥጢር[፫] አሳድሪብን[፪]
ኧኸ እንማልድሻለን[፪] እመቤታችን
እንድትባርኪልን[፫] ስብሰባችንን በዓላችንን[፪]

## ክሊባኖስ (32)

ክሊባኖስ[፪] ከልጅሽ ጋር ነዩ
እመ አዶናይ ክሊባኖስ ወደእኛ ነዩ
ጥበቃሽ ዘወትር ክሊባኖስ እንዳይለየኝ ክሊባኖስ
በሄድኩበት ሁሉ ክሊባኖስ ማረፍያ ሁኚኝ ክሊባኖስ
እዝ…
እኔን ባርያሽን ክሊባኖስ ድንግል አትርሺኝ ክሊባኖስ
በጽድቅ ስሌዳ ክሊባኖስ ስሜን ጻፊልኝ
እዝ…
ነፍስና ሥጋዬን ክሊባኖስ አደራ እልሻለሁ ክሊባኖስ
በልጅሽ ጽኑ ፍቅር ክሊባኖስ ተማፅኘሻለሁ ክሊባኖስ
እዝ…
ከመሞቴ በፊት ክሊባኖስ ለንስሐ አብቂኝ ክሊባኖስ
ለነፍሴ ማደርያ ክሊባኖስ አዘጋጂልኝ ክሊባኖስ
እዝ…
የልብሰሽ መዓዛ ክሊባኖስ የሊባኖስ ሽታ ክሊባኖስ
ሮማን ናርዶስ ነሽ ክሊባኖስ እናቱ ለጌታ ክሊባኖስ
እዝ…
እመቤቴ ስልሽ ክሊባኖስ ስምሽን ስጠራ ክሊባኖስ
ፈጥነሽ ድረሺልኝ ክሊባኖስ ከቅዱሳን ጋራ ክሊባኖስ
ፈጥነሽ ድረሺልኝ ክሊባኖስ ከሚካኤል ጋራ ክሊባኖስ
ፈጥነሽ ድረሺልኝ ክሊባኖስ ከገብርኤል ጋራ ክሊባኖስ
ፈጥነሽ ድረሺልኝ ክሊባኖስ ከሡርኤል ጋራ ክሊባኖስ
እዝ…

## ሰምኚ (33)

ሰምኚ ድንግል ሰምኚ[፪]
ለኃጥአን[፫] አይደለም ለጻድቃን
ሰምኚ ታላቅ ስጦታዬ ሰምኚ እዛኝ ርኅሩኅ ነሽ
ሰምኚ የጌታዬ እናት ሰምኚ ጸጋን የተመላሽ
ሰምኚ የአምላክ ማደርያ ሰምኚ ለምነሽ አስምሪኝ
ሰምኚ እማናዊት ጽዮን ሰምኚ ከእኔ አትለዪኝ
አዝ...
ሰምኚ ኀዘንሽ ኀዘኔ ሰምኚ ለእኔ ይሁን ድንግል
ሰምኚ የተንከራተትሽው ሰምኚ በሀገረ እስራኤል
ሰምኚ ትዕግሥትሽን ሳየው ሰምኚ ልቤ ይመሰጣል
ሰምኚ የኀዘን እምባ ጎርፍ ሰምኚ ዓይኔን ይሞላዋል
አዝ...
ሰምኚ በቀራንዮ እምባ ሰምኚ በእዛ የፍቅር ዐታ
ሰምኚ እግረ መስቀሉ ሥር ሰምኚ ከክርስቶስ ጌታ
ሰምኚ ለእኛ ተሰጥተሻል ሰምኚ እናት እንድትሆኚን
ሰምኚ ልጆችሽ ነንና ሰምኚ ምልጃሽ አይለየን
ሰምኚ ልጆችሽ ነንና ሰምኚ ፍቅርሽ አይለየን
አዝ...
ሰምኚ እንደበቱን ጌታ ሰምኚ በምስጋና ሙላው
ሰምኚ ደስ ይበልሽ ብዬ ሰምኚ እኔም ላመስግናት
አዝ...

## እመቤታችን ለአንቺ (34)

እመቤታችን ለአንቺ ሰላምታ ይገባሻል[፪]
ከሴቶች ሁሉ[፫] ተመርጠሻል
ሐርና ወርቁን እያስማማች ስትፈትል[፪]
ተዘጋጀላት[፫] የመመረጥ ዕድል
አዝ...
እያረጓጓት የሰማይ መላእክት[፪]
ቤተ መቅደስ ኖረች[፫] እሥራ ሁለት ዓመት
አዝ...
መንፈስ ቅዱስ እንደቀረባት አውቆ
ሰገደላት[፫] ዘካርያስ ታጥቆ
አዝ...
መንፈስ ቅዱስ እንደቀረባት አውቃ
ተሳለመቻት[፫] ኤልሳቤጥም ታጥቃ
አዝ...
እያስደንቀንም ወይ የማርያም ትሕትና[፪]
ውኃ ስትቀዳ[፫] የአምላክ እናት ሆና
አዝ...
የምንጭ ውኃ ምሥጢር የሚያመለክተው[፪]
የአምላክ መገኛ ምንጭ[፫] እሷ መሆኗን ነው
አዝ...

## ነይ ነይ ማርያም (35)

ነይ ነይ ማርያም ወላዲተ አምላክ
የጻድቃን እመቤት የመላእክት እኅት

ሁላችሁ እመኗት ከልብ
እማላጅ ናትና በእውነት
እናመስግናት እናወድሳት
እማላጅ ኪዳነ ምሕረት

## ሰላም ለአንቺ ይሁን (36)

ሰላም ለአንቺ ይሁን[፫] ማርያም ድንግል[፪]
የሴቶች መመኪያ የሴቶች[፪] አክሊል[፪]
ሰላም ለአንቺ ይሁን[፫] የሁሉ እመቤት[፪]
የኃጥአን ተስፋ የጻድቃን[፪] ሕይወት[፪]
ሰላም ለአንቺ ይሁን[፪] የሁሉ ወዳጅ[፪]
የጽድቅ መሰላል የዓለም[፪] አማላጅ[፪]
ሰላም ለወለድሽው[፫] ለአምላካችን[፪]
ሰማይና ምድር የማይችሉትን[፪]
ሰላም እመቤቴ[፫] አምላክን የወለድሽ[፪]
የሰማይ መላእክት የሚያመሰግኑሽ[፪]
ሰላም ለእመቤቴ[፫] አምላክ የመረጠሽ[፪]
ከሴቶች ሁሉ የተባረክሽ[፪] ነሽ[፪]

## ኪዳነ ምሕረት (37)

ኪዳነ ምሕረት እመቤት
የዓለም ሁሉ መድኃኒት
ቅድስተ ቅዱሳን ንጽሕት
አንቺ ነሽ የአምላካችን እናት
ጌታ አንቺን ፈጠረሽ ልዩ አድርጎ
በሚያስደንቅ ምሥጢሩ ተዋሕዶ
ስልዑል ማደርያነት የተመረጥሽ
ያለህማም ወለድሽው ድንግል ሆነሽ

እናትነት ድንግልና
አስተባብረሽ ይዘሻልና

ድንግልም እናትም እመ ብርሃን
ቅድስተ ቅዱሳን እኛን እማልጂን

## ወተቀውም ንግሥት (38)

**ወትቀውም ንግሥት (2) በየማንከ (2)**
**በአልባስ ወርቅ (2) ዑጽፍት ወሑብርት**

**ትርጉም፦ በወርቅ መጐናጸፊያ ተጐናጽፋ ንግ ሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች**

## ማርያም ዐረገች (39)

ማርያም ዐረገች[፪] ወደ ገነት
የሰማይ መላእክት በደስታ እያጀቧት[፪]

## ኪዳነ ምሕረት ለመንኩሽ አንቺን (40)

ኪዳነ ምሕረት ለመንኩሽ አንቺን
እንድታማልጂኝ[፫] ከፈጣሪያችን
መጣች በደመና ማርያም ድንግል
ልታማልደን[፫] ከፈጣሪ ጋር

## ኪዳነምህረት (41)

**ኪዳነ ምህረት ለመንኩሽ አንቺን**
**ልታማልጂኝ (3) ከፈጣሪ ጋር**
**መጣች በደመና ማርያም ድንግል**
**ልታማልደን (3) ከፈጣሪ ጋር**

www.ethiopianorthodox.org

## ኪዳነ ምሕረት እናቴ (42)

ኪዳነ ምሕረት እናቴ አማልጂኝ እኔን ከልጅሽ
የፍቅር እናት ነሽና አማልጂኝ እኔን ከልጅሽ
የሰላም እናት ነሽና አማልጂኝ እኔን ከልጅሽ
የተገለጠው ብርሃን በምሥራቅ የተወለደው
በፍቅር ሰንሰለት አስሮ ዓለምን ሁሉ አዳነው[፪]
አዝ...
በረሀውን በአሰኩበት ጊዜ የግብጽን የአሸዋ ግለት
አንቺ ትንሽ ብላቴና ኸረ እንዴት ቻልሽው በእውነት[፪]
አዝ...
ዝም ብዬ ይደንቀኛል የአምላክን ሥራ ሳስበው
ምክንያት አንቺን አድርጎ ይህንን ዓለም አዳነው[፪]
አዝ...

## አምላክ ለእኛ ብሎ (43)

አምላክ ለእኛ ብሎ ቃል ኪዳን የሰጣት
የኃጥአን አማላጅ ኪዳነ ምሕረት ናት[፪]
ከአንቺው በተገኘው በቅዱሱ ፍሬ
ዓለም ተቀድሷል ይኸውና ዛሬ[፪]
ካህናት በክበር ሲያመሰግኑሽ
እኛም በጭብጨባ እንዘምርልሽ[፪]
እንደአማለድሽው በላዔ ሰብእን
እኛንም እባክሽ አደራ አማልጂን[፪]
ስምሽ ግርማ ያለው ኪዳነ ምሕረት
የኃጥአን ተስፋ የጌታዬ እናት[፪]

## መሠረተ ሕይወት (44)

መሠረተ ሕይወት ማርያም
ወጥንተ መድኃኒት ዘእምቀዲሙ (2)
ለወልድኪ (2) አምሳለ ደሙ (2)

ትርጉም፦ ቅድመ ዓለም የነበረ መድኃኒት ከሚ
ባል የተገኘሽ የሕይወት መሠረት
ማርያም አንች ነሽ። መሠረትነት
ሽም የልጅሽ የደሙ ምሳሌ ነው።

## ምሥራቀ ምሥራቃት (45)

ምሥራቀ ምሥራቃት መዐዛ ፀሐይ እግዚአትየ
ዘመና መዓዛይ[፪]
ዘመና መዓዛይ ማርያም ዘመና መዓዛይ[፬]

የኅብስት ክርስቶስ መገኛ የወርቅ
መሶብ ከፀሐይ መውጫዎች ሁሉ
የምትበልጭ የፀሐይ መውጫ አንቺ ነሽ

## ቅድስተ ቅዱሳን (46)

ማርያም ድንግል ቅድስተ ቅዱሳን[፪]
ለምኝልን አማልጅን ጸልይልን ወደ ጌታችን[፪]

## ድንግል ማርያም ኀዘነ ልቡና (47)

ድንግል ማርያም ኀዘነ ልቡና ታቀልል[፪]
ኀዘነ ልቡና[፬] ታቀልል

ድንግል ማርያም የልብን ኀዘን ታቀላለች[፪]
የልብን ኀዘን[፬] ታቀላለች

## ተናዘዘብኪ (48)

ተናዘዘብኪ እኮኑ ሕሊና ቀዳማይ አብ (2)
ኪዳነ ምሕረት ማርያም (2)
ኪዳነ ምሕረት ማርያም ኪዳነ አምላክ

ቸርጉም፦ አምላክ ቃል ኪዳን የሰጠሽ እመቤታ
ችን ነሽ ስላንቺ ተነግሮልሻልና ቃል
ኪዳን የተቀበልሽ ነሽ።

## ታማልደናለች (49)

ታማልደናለች (2) ማርያም (2) ቤዛዊት ዓለም
ሚካኤል በክንፉ ገብርኤል በፋና
ያወጡናል (2) ከሲኦል ፈተና

## ሐመልማላዊት ዕፅ (50)

ሐመልማላዊት[፫] ዕፅ
ሙሴ ዘርአያ[፪] በደብረ ሲና
ደብረ ሲና ማኅደረ ስብሐት

እመቤታችን ሆይ የምስጋና ማደርያ
የምትሆን በሲና ተራራ ሙሴ ያያት
ለምለም ዕፅ አንቺ ነሽ

## ኦ ርኅርኅተ ኅሊና (51)

ኦ ርኅርኅተ ኅሊና እፍቅሮተ ሰብእ ልማዳ
ስዕለ ጌሠመ[፬] ትመሰል[፫] እንግዳ

ሰውን በማፍቀር የኅሊና ርኅራኄ ልማድ
ያለሽ በየቀኑ በየዕለት እንግዳ ትመስያለሽ

## ለትለይን (52)

አትለይን (2) ድንግል ሆይ ድረሽልን (2)
ከዲያብሎስ እጅ አንቺ አድኚን
ምሕረት ከልጅሽ ለምኚልን(2)

www.ethiopianorthodox.org